# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!




በኮንፈራንሱ ላይ ሁላችንም በመገኘት የበረከቱ ተካፋዮች እንሁን። ሌሎች ሰዎችንም እንድትጋብዙ እናበረታታለን። የሚጀምረው የፊታችን አርብ (April 27 @ 6:30p.m.) ነው። ቅዳሜ ደግሞ (April 28 @ 3:00p.m.) ይሆናል። እሁድ በመደበኛ የአምልኮ ሰአታችን ይቀጥላል።

"ወደ ውጭም አውጥቶ:- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም:- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

**ሸማግሌዎችን ለማግኘት:-**

773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

# የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2:10




"ኑ፥ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን፤ ለአምላክ ለመድኃኒታችን እልል እንበል።" (መዝ. 95:1)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**April 22, 2018**

**ሚያዚያ 14፤ 2010 ዓ.ም.**

## የእሁዱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም ጌቱ ጳውሎስ |
| አምልኮ....................... | የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም አያሌው አስፋው |
| ቃል ............. | እህት ሰናይት ከበደ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

# "እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።"

(ዕብ. 11:1)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመን | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### <u>በእምነት መቅረብ</u>

*"ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና።" (ዕብ. 11፡ 6)*

አባታችን ሄኖክ በትውልዱ መካከል ለየት ያለ ሰው እንደነበረ መጽሐፍ ያስተምረናል። የትውልዶችን የዘር ሃረግ የያዘውን ዘፍጥረት ምዕራፍ ስድስትን ስናነብ የብዙ አባቶች ህይወት የተዘገበው "እገሌ ይህን ያህል አመት ኖረ፣ ወንድኖችና ሴቶች ልጆችን ወለደ፣ ሞተም" እየተባለ ነው። ነገር ግን ሄኖክ ላይ ስንደርስ አተራረኩ ለየት ይላል። ስለ ሄኖክ ሲናገር "ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ...ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፣ እግዚአብሔር ወስዶታልና" በማለት በትውልዶች መካከል ለየት ያለውን የሄኖክን ሕይወት መጽሐፍ ይተርክልናል። (ዘፍ. 5፡21-24) የዕብራዊያን ጸሓፊ ደግም ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገው እንዴት እንደሆነ በመንፈስ ቅዱስ ብረሃን ያስረዳናል። (ዕብ. 11፡ 5-6)

ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገው በእምነት በመመላለስ ነበር። በእምነቱ እግዚአብሕሔርን ደስ አሰኝቷል። ከዚህም የተነሳ በእምነት የሚገኝ ሕይወት ምሳሌ ሆኖ ሞትን አልቀመሰም። በዘመኑ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ፍጻሚያቸው ሞት ነበር። ሄኖክ ግን "ሞትን እንዳያይ በእምነት ተወሰደ።" ሄኖክ በዘመኑ ሞትን ሳይቀምስ የተወሰደው በእግዚአብሔር ላይ ከነበረው እምነት የተነሳ ነው። ወገኖቼ፡- ዛሬም በክርስቶስ በማመን ከሞት ወደ ሕይወት በተሸጋገርን በኛ ላይ ሞት ስልጣን የለውም። የሄኖክ እምነት በሕወቱ ላይ ለውጥ ያመጣ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርም ደስ የተሰኘበት እምነት ነበር። መቼም መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስናጠና ከምንረዳው ቁም ነገር አንዱና ዋንኛው እግዚአብሔር እርሱን አምነው በሚመላለሱ ሰዎች እንዴት ደስ እንደሚሰኝ ነው። ለዚህ ዋቢ ይሆነን ዘንድ በዕብራዊያን ምዕራፍ 11 ላይ የተዘረዘሩትን የእምነት አርበኞች ማስታወሱ በቂ ነው። ጌታ ኢየሱስም በምድር ሲመላለስ አስደንቀውት ከነበሩት ነገሮች አንዱና ዋንኛው ባልጠበቀው ስፍራ በሰዎች ያገኘው እምነት ወይንም ሊያምኑ በተገባቸው ሰዎች ያጣው እምነት ነበር። ለመሆኑ ከአባታችን ሄኖክ እምነት የምንማረው ምንድን ነው?

የሄኖክ እምነት መሰረታዊ አስተምሮ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ እግዚአብሔር እንዳለ ያምን ዘንድ እንደሚያስፈልገውና እግዚአብሔርም በእምነት ለሚፈልጉት ዋጋ እንዲሚሰጥ ማመን ናቸው። ይህ አይነቱ እምነት የእግዚአብሔርን ሕልውና የመቀበል ጉዳይ ብቻ አይደለም። ብዙ ሰዎች (ሰይጣንም ጭምር) እግዚአብሔር እንዳለ ግንዛቤ ወይንም እውቀት አላቸው። ነገር ግን ያ እወቀት ሕይወታቸውን (ልባቸውን) የሚገራ እውቀት ሳይሆን የአእምሮ እውቀት ብቻ ነው። ከሄኖክ የምንማረው እምነት ግን ከዚህ የሚያልፍ ነው። ሄኖክ እግዚአብሔር እንዳለ ሲያምን እግዚአብሔርን በሚፈልገው ጉዳይ እንዳለ ነው የሚያምነው። በጤናው ላይ እግዚአብሔርን ሲያምን እግዚአብሔር ፋዋሽ አምላክ እንደሆነና እንደሚፈሰው ነው የሚያምነው። በፋይናንሱ ላይ እግዚአብሔርን ሲያምን እግዚአብሔር የሚባርክ አምላክ እንደሆነና ሊባርከው እንደሚችል ነው የሚያምነው። በጥበቃው ላይ እግዚአብሔርን ሲያምን እግዚአብሔር እንደሚጠብቀውና ከአውሬና ከክፉ ወጥመድ ሁሉ እንደሚታደገው ነው የሚያምነው። እንግዲህ ሄኖክ ያመነው የእግዚአብሔርን ሕልውና፣ አዳኝነት፣ ፈዋሽነት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር እርሱን በፈለገበት በዚያ ማንነቱ እንደሚገለጥለትና ዋጋም እንደሚሰጠው ጭምር ነው።

ወገኞቼ፡- ክርስትና የእምነት ጉዞ ነው። ወደ እግዚአብሔር የምንቀርበውና እግዚአብሔርን ደስ የምናሰኘው በእምነት ብቻ ነው። ዛሬ በማናቸውም በፊታችን ባለ ጉዳይ ላይ እግዚአብሔርን እየፈለንግ እርሱን በፈለግንበት አቅጣጫ ሁሉ ላይ ዋጋ እንደሚሰጠን በማመን እንመላለስ። አሜን!